የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN
COMMUNICATIONS AUTHORITY

የ ቴሌኮሙኒኬሽን ሙግት መፍቻ መመሪያ

ቁጥር 796/2013

2013 ዓ.ም

የቴሌኮሙኒኬሽን ሙግት መፍቻ መመሪያ

በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች እና ተጠቃሚዎች እንዲሁም በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የሚነሳ አለመግባባቶችን ፍትሃዊ፣ ፈጣን እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መፍታት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ ወስጥ የሚነሱ አለመግባባቶችን ማስተዳዳር የሚያስችል በቂ የህግ ማዕቀፍ ማበልጸግ አስፈላጊ መሆኑን በሚዳት፤

ለተከራካሪ አከላት አማራጭ የግጭት መፍቻ ስነ ስርሃቶችን ማለትም ድርድር እና ሽምግልናን የማሰሰሉትን ማዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን በማንዘብ፤

በኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ አንቀጽ 6 (2) ፥6 (15) ፥37፥ 48 እና 54(2) ማስረት ባለስልጣኑ ይህንን የቴሌኮሙኒኬሽን ሙግት መፍቻ መመሪያ አወጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሙግት መፍቻ መመሪያ ቁጥር 796/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፤

1) **"ይግባኝ ሰሚ አካል"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 39 የተቋቋመው የይግባኝ ሰሚ አካል ነው፤
2) **"ባለሥልጣን"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 3 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፤
3) **"ከሣሽ"** ማለት በባለሥልጣኑ ዘንድ ክስ የመሠረተ ሰው ነው፤
4) **"ተጠቃሚ"** ማለት የባለፍቃዱን የአገልግሎት ማስጫ ስምምነት በመፈረም ወይም በባለፍቃዱ የቀረበትን የወል ሁኔታዎች በመቀበል የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚያገኝ ማንኛውም ሰው ነው።
5) **"ቅሬታ"** ማለት በመደበኛ መንገድ በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መበቴ ተጥሷል በሚል በከሳሽ የሚቀርብ ክስ ነው፤
6) **"አለመግባባት"** ማለት ፈቃድ ባላቸው አከላት እንዲሁም በባለፍቃድ እና በተጠቃሚ መካከል አንዱ በሌላኛው ወገን ተግባር ወይም ወሳኔ ሲከፋ ወይም ሁለቱም ወገኖች እርስ በእርስ በወሰዱት ወሳኔ ወይም በፈጸሙት ተግባር ሲከፉ እና ጉዳዩን ለመፍታት ተገቢ ጥረት አድርገው ስምምነት ላይ መድረስ ያለቻሉበት አጨቃጫቂ ጉዳይ ነው።
7) **"ፈቃድ"** ማለት በባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ነው፤
8) **"ባለፈቃድ"** ማለት በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሠጠው ሰው ነው፤
9) **"የወሳኔ ማስወቂያ"** ማለት ባለፈቃዱ ለአቤቱታ መፍትሄ በማስጠት ወይም አቤቱታን ባለመቀበል በጽሑፍ ወይም በሌላ በማንኛውም ሊረጋገጥ በሚችል ዘዴ የሚሰጠው የሚጨርሻ ወሳኔ ነው፡፡

10) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡ በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴት ጾታም በእኩል ያገለግላል፡፡

11) **"ይፋ ማድረግ"** ማለት ባለሥልጣኑ የሰጠውን ውሳኔ በድረ-ገጹ እና/ወይም አግባብ ባለው ሌላ ዘዴ ማገለጽ ነው፤

12) **"ማት መፍትሔ እንዲያገኝ የማቅርብ ጥያቄ"** ማለት ባለሥልጣኑ አለመግባባትን እንዲመረምርና መፍትሔ እንዲሰጥ በአቤቱታ አቅራቢ የማቅርብ ጥያቄ ነው፡

13) **"ሜልስ ሰጪ"** ማለት ክስ የቀረበበት ወገን ወይም በከሣሽ ለቀረበ ክስ ሜልስ የሚሰጥ ሰው ነው፤

14) **"ሜልስ"** ማለት የቀረበውን ክስ በተማለከተ ወይም ከባለሥልጣኑ ለቀረበ ጥያቄ ለባለሥልጣኑ የማቅርብ የጽሑፍ ሜልስ ነው፤

15) **'ማድረስ'** ማለት እንደሁኔታው ሰነዶች፥ ኢንፎርሜሽን ወይም ዳታን ለሌላኛው አካል ወይም ለባለስልጣኑ በሚደበኛ አስተላላፊዎች፥ በተማዘገበ ፖስታ፥ በኤሌክትሮኒክ ሜል እና/ወይም ፋክስ ወይም ሌላ አግባብነት ባላቸው አካላት መካከል እና በባለስልጣኑ መካከል ስምምነት በተደረገበት መንገድ ማድረስ ነው፡፡

16) **'የስራ ቀናት'** ማለት ስራ የሚከራባቸው ቀናቶችን ብቻ የሚማለከት ሲሆን ቅዳሜ እሁድ፥ እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ባሕላት ተብለው የተለዩ ቀናቶችን አይጨምርም፡፡

3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማዎች፡ -

1) በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች እና ተጠቃሚዎች እንዲሁም በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የሚነሳ አለመግባባቶችን መፍታት የሚያስችል ማቀፍ በማበልጸግ አለመግባባቶችን ፍትሃዊ፣ ፈጣን እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መፍታት፤
2) ባለስልጣኑ አለመግባባቶችን የሚፈታበት ስነስርሃቶች ላይ ግልጽነትን መፍጠር፤ እና
3) ለተከራካሪ አካላት አማራጭ የግጭት መፍቻ ስነስርሃቶችን ማለትም ድርድር እና ሽምግልናን የማስሰሉትን ማዘርጋት ፤

ናቸው፡ ፡

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ባገኙ በሁሉም ባለፈቃዶች፣ እና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡ ፡

ክፍል ሁለት
ማትን ስለመፍታት

5. ማትን ለመፍታት ባለሥልጣኑ ስላለው ሥልጣን

1) ባለሥልጣኑ ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት አካላት መካከል የሚነሱ ማቶችን የመፍታት ሥልጣን አለው፤

ሀ) በተጠቃሚዎችና በባለፈቃዶች መካከል፤ እና

ለ) በባለፈቃዶች መካከል፡፡

2) ባለሥልጣኑ ከተጠቃሚዎች በሚቀርብ ቅሬታ መሠረት የስልጣን ገደቡ ወስጥ በሆነ በማንኛውም ጉዳይ ወይም በማንኛውም ወገን መፍትሔ ለማግኘት በሚቀርብ ጥያቄ ላይ የአዋጁን ዓላማ በተሻለ ሁኔታ ለሚፈጸም ይረዳል የሚል እሳቤ ካለው በባለፈቃዱ ላይ ምርመራ ሊጀምር ይችላል፡፡

3) የባለሥልጣኑ ወሳኔ በማንኛውም ጉዳይ እና በማንኛውም ወገን መፍትሔ ለማግኘት የቀረበ ጥያቄን በሙሉ ወይም በከፊል ሊቀበለው፣ ወድቅ ሊያደርገው ወይም በባለሥልጣኑ የስልጣን ገደብ ወስጥ የአዋጁን ዓላማ በተሻለ ሁኔታ ለሚፈጸም የሚያስችል ሌላ መፍትሄ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4) የባለስልጣኑ ወሳኔዎች በአዋጁ አንቀጽ 38 መሰረት በድጋሚ ሊታዩ ይችላሉ።

6. የባለሥልጣኑ መዛግብትን እንዲጣመሩ የማድረግ ሥልጣን

1) ባለሥልጣኑ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ክሶች ላይ አንድ ወሳኔ ማስጠት የሚያስችሉ የሚከተሉ ሁኔታዎችን ግምት ወስጥ በማከተት በአንድነት እንዲታዩ ሊያደርግ ይችላል፤

ሀ) አለመግባባቶቹ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ከሆኑ እና አመቺ በሆነ ሁኔታ እንደ አንድ ነጠላ ክርክር ማየት ከተቻለ፤ እና

ለ) በተጠቃለሉት የክርክር መፍቻ ሂደቶች በሁሉም ደረጃዎች ባለጉዳዮቹ ተመሳሳይ ፍላጎት የሚኖራቸው ከሆነ፤

2) በዚህ አንቀፅ ንሁስ አንቀጽ 1(ሀ) እና 1(ለ) ያሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ፤ ተጠቃሚዎች የጋራ ክሳቸወን እንደ አንድ ክስ አደረገው ሊያቀርቡት ይችላሉ።

3) አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ባለጉዳዮች ባለስልጣኑ ክሱ ይጣመር ብሎ የወሰነወን ወሳኔ ከተቃወሙ ባለስልጣኑ ለተቃወሞ ምክንያት የሆነወን የክርክር ነጥብ ሊመለከተው ይችላል።

4) ባለሥልጣኑ የተጣመሩ ክርክሮችን በማየት ላይ ባለበት በየትኛውም ደረጃ ክርክሮቹ ተጣምረው መታየት የለባቸውም የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሰ ክርክሮቹን በተናጥል ማስማቱን ሊቀጥል ይችላል፡፡

ክፍል ሦስት

መፍት መፍትሔ እንዲያገኝ ስለማጠየቅ

7. መፍት መፍትሔ እንዲያገኝ ስለማጠየቅ

1) ባለፈቃዶች መፍታቸው አንዲፈታላቸው ለባለስልጣኑ ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት ልዩነታቸውን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ተገቢ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

2) መፍቱ መፍትሔ እንዲያገኝ የሚፈልግ ወገን (ከዚህ በኋላ "ከሣሽ") ፤

ሀ) በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው እና በባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ ላይ የሚገኘውን ቅጽ በመሙላት እና

ለ) የክሱን ግልባጭ ለሌላኛው ወገን (ከዚህ በኋላ "ሚሰስ ሰጭ") በማድረስ፤

ክሱን መጀመር ይችላል፡፡

3) ተከራካሪ አካላት ልዩነታቸውን በአማራጭ ሙግት ዘዴ መፍታት እስካልጀመሩ ድረስ፤ በባለፍቃዶች መካከል ክርክር ሲነሳ ከሳሽ የክሱ ምክንያት በጀመረ በሰላሳ (30) የስራ ቀናት ወስጥ ክሱን ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት።

4) ከሳሽ የሚያቀርበው ክስ የሚከተሉትን ነገሮችን አካቶ ማያዝ ይኖርበታል፤

ሀ) የተከራካሪ ወገኖች ስም፣ አድራሻ እና የስልክ ቁጥር፤

ለ) የክርክሩን ባህሪ የሚያሳከት መግለጫ

ሐ) የገንዘብ ማጠንን ጨምሮ የሚጠየቀውን መፍትሔ ወይም ዳኝነት፤

መ) ባለስልጣኑ ጉዳዩን ተቀብሎ የማየት የህግ ሥልጣን ያለው መሆኑ፤

ሠ) ጉዳዩን ሊያስረዱ የሚችሉ ደጋፊ ማስረጃዎች፤ እና

ረ) ሌላ ማናቸውም አግባብነት ያላቸውን ሚጃዎችን፤

5) ባለሥልጣኑ ክሱን በተቀበለ በአምስት (5) የስራ ቀናት ወስጥ የክሱን መድረስ ለከሳሽ እና ለሚልስ ሰጭ ማሳወቅ አለበት፡፡

6) ክርክሩ ብዛት ያላቸው ወገኖችን የሚያሳከት ከሆነ ከሳሹ ለባለሥልጣኑ የቀረበትን ሰነዶች ቅጇዎች በሙሉ ሰነዶቹ ለባለሥልጣኑ በቀረበበት ቀን ወይም ከዚያ በፊት ለሌሎቹ ወገኖች በሙሉ እንዲደርሳቸው ማድረግ አለበት፡፡

7) ተከራካሪ ወገኖች በክሱ ከተማከከቱት ምክንያቶች ውጭ ያሉ ምክንያቶችን ማቅረብ ወይም በክሱ ያልተጠቀሱ ተጨማሪ ፍሬ ነገሮችን ወይም ሰነዶችን መጥቀስ ወይም ከክሱ ጋር ያልተያያዙ የሰነድ ቅጇዎችን ማቅረብ አይችሉም፡

8. ሙግት መፍቻ ጥያቄን ወድቅ ስለማድረግ

1) ባለሥልጣኑ ሙግት መፍቻ ጥያቄን በሚከተሉት ሁኔታዎች ወድቅ ሊያደርግ ይችላል፤

ሀ) ጥያቄው ከባለሥልጣኑ የሥልጣን ገደብ ውጭ የሆነ የህግ ጉዳዮችን የሚያስነሳ ወይም የሚይዝ ወይም በአዋጁ በባለሥልጣኑ መፍትሔ እንዲሰጥበት ያልተማከከተ ከሆነ፤

ለ) ከባለፈቃድ ጋር ያለ ሙግት መፍትሔ እንዲያገኝ የሚቀርብ ጥያቄ ባለፈቃዱ በተጠቃሚዎች መብትና ጥበቃ መመሪያ በተማከከተው መሠረት "የወሳኔ ማስታወቂያ" ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት በሠላሳ (30) የስራ ቀናት ወስጥ ያልቀረበ ከሆነ፤

ሐ) ጉዳዩን የሚያሚምረው ፍርድ ቤት ባለሥልጣኑ ጉዳዩን እንዲያየው ካልጠየቀ በስተቀር፤ መፍትሔ እንዲሰጥበት የቀረበው ክርክር በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ባለ ፍርድ ቤት በመታየት ላይ የሚገኝ ከሆነ፤

መ) ጥያቄው ርዕስ አንቀጽን፣ ሥነ ጽሑፍን፣ ፊጠራን፣ ፖለቲካን፣ ኃይማኖትን ወይም ሌሎች በባለፈቃዱ የኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሥርዓት የሚገለጹ ወይም የሚተላለፉ ሌሎች ጉዳዮችን ጨምሮ የኮሚኒኬሽን አገልግሎት ይዘት ያለው ከሆነ፤

ሠ) ጥያቄው ያልተሟላ ወይም በዚህ መመሪያ በተማከከቱት ሥርዓትና ማስፈርቶች መሠረት ያልቀረበ ከሆነ፤

2) ባለሥልጣኑ ክሱን ላለመቀበል ከመወሰኑ በፊት ለከሳሹ የማስማት ዕድል ማጠት አለበት፡፡

3) የዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሠ) ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ ክሱን ለመሠረተው ሰው ያላሟላውን ነገር በአሥር (10) የስራ ቀናት ወስጥ እንዲያሟላ ዕድል ሳይሰጠው ክሱን ወድቅ ማድረግ አይችልም፡፡

4) ባለሥልጣኑ በክርክሩ ላይ ወሳኔ ላለማስጠት ከወሰነ፤ የቀረበውን ክስ ያልተቀበለበትን ምክንያት በመግለጽ ለባለጉዳዮቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

9. ስለክስ መልስ እና ስለተከሳሽ ከሳሽ ክስ

1) መልስ ሰጪው ክሱ በደረሰው በአስር (10) የሥራ ቀናት ወስጥ መልሱን እና ማንኛውም ደጋፊ ሰነዶችን ለከሳሽና ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

2) በመልስ ሰጪው የሚቀርብ መልስ የሚከተሉትን ነገሮች መያዝ አለበት፤

ሀ) የመልስ ሰጪውን ስም፣ አድራሻ እና ሌሎች መግለጫዎች፤

ለ) ለክሱ የሚሰጠውን መልስ እንዲሁም የተከሳሽ ከሳሽ ክስ ካለ፤ እና

ሐ) ሌላ ማናቸውም አግባብ የሆኑ ሚዲያዎች፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በከሳሽ የሚቀርብ መልስ በመልስ ሰጪው መልስ ወይም የተከሳሽ ከሳሽ ክስ ላይ በተነሱ ነጥቦች መወሰን አለበት፡፡ ምንም ዓይነት አዲስ ጉዳዮች ሊካተቱ አይችሉም፡፡

10. ሰነዶችን ስለማቅረብ

ከባለጉዳይ ለባለሥልጣኑ በፅሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ የሚቀርቡ ሰነዶች ባለሥልጣኑ ሰነዶቹን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በባለሥልጣኑ እንደተመዘገበ ይቆጠራል፡፡

ክፍል አራት
ስለክስ ማሰማት

11. የክስ ማሰሚያ ሰዓትና ቦታ

1) ባለሥልጣኑ ለየትኛውም ባለጉዳይ ክርክሩ እንዲሰማ የማጠየቅ መብት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ወሳኔ በጽሑፍ ላይ ብቻ የተመሠረተ እንዲሆን የማድረግ ሥልጣኑ የተጠበቀ ነው፡፡

2) ባለስልጣኑ ክሱ ማሰማት አለበት ብሎ ከወሰነ፤ ይህኑ ለባለጉዳዮች በጽሑፍ ያሳወቃቸዋል።

3) ባለስልጣኑ ባለጉዳዮችን በእኩልነት፥ በፍትሃዊነት እና ጉዳያቸውን ለማስረዳት ሙሉ እድል በሰጠ መልክ እስካስተናገዳቸው ድረስ የማሰማት ሂደቱን አግባብ ነው ብሎ በሚያስበው መንገድ ሊያከናውን ይችላል።

4) ባለሥልጣኑ ክሱ የሚሰማበትን ቀንና ቦታ እንዲሁም ክሱ የሚሰማበት ሂደት የሚፈጀውን ጊዜ ለባለጉዳዮቹ ማሳወቅ አለበት፡፡

5) ባለስልጣኑ ክሱ የሚሰማበትን ቀንና የሚፈጀውን ጊዜ ለመወሰን የጉዳዩን ወስብስብነት እና ጉዳዩ በተፋጠነ ሁኔታ ባይወሰን በባለጉዳዮቹ ላይ ሊደርስ የሚቻለውን ጉዳት ከግምት ወስጥ ማስገባት አለበት፡፡

6) ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸው በባልሥልጣኑ መፍትሔ እንዲያገኝ አስፈላጊውን ሁሉ አጠናቀው ለባለሥልጣኑ ባቀረቡ ከአስራ አምስት (15) የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ክሱ ማስማት መጀመር አለበት፡

12. ለሕዝብ ክፍት ስለማድረግ

1) በባለሥልጣኑ የሚከሄደው ክስ የማስማት ሂደት ክሱ በሚሰማበት ወቅት ከሚታየው ጉዳይ ሚስጥራዊነት ባህሪ የተነሳ ለህዝብ ይፋ መሆን እንደሌለበት በባለሥልጣኑ ካልተወሰነ በስተቀር ለሁሉም ሰው ክፍት መሆን አለበት፡፡

2) ባለስልጣኑ የጉዳዩን ሚስጥራዊነት ሲወስን በጉዳዩ ላይ ተሳታፊ የሆኑ አካላት አስተያየት ሊጠይቅ ይችላል።

3) ባለሥልጣኑ በማንኛውም የክስ ሂደት የሚረጃ ተደራሽነትን ከህዝቡ የሚገድብበትን ምክንያት ለሕዝብ ማሳወቅ እና በተቻለ ማጠን ሁሉም የክስ ማስሚያ ሂደቶች ሙሉ በሙሉ ለህዝብ ክፍት መሆናቸውን ለሚረጋገጥ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

13. በክርክር ማስማት ሂደት ስለሚቀርብ ባለሙያ

ለመገት መፍትሄ በማስጠት ሂደት በባለስልጣኑ አስተያየት የተወሰነ ዕወቀት ወይም ብቃት የሚጠይቅ ጉዳይ ያጋጠመ እንደሆነ፤ ባለስልጣኑ በሙያው ዕወቀት ያለው፥ ገለልተኛ፥ እና ከማንኛውም የጥቅም ግጭት ነጻ የሆነን ሰው በገምጋሚነት እንዲያግዘው ሊጋብዘው ይችላል።

14. ምስክርን ስለመመርመር

1) ባለሥልጣኑ ክርክርን በሚሰማበት ጊዜ ተከራካሪ ወገኖችን እና ምስክሮቻቸውን ለሚረምር ይችላል፡፡

2) ከሁለቱ በአንዱ ተከራካሪ የተጠራና የተመረመረ ምስክር በሌላኛው ተከራካሪ ማስቀለኛ ጥያቄ ሊጠየቅ ይችላል፡፡ ምስክሩ ማስቀለኛ ጥያቄ ከተጠየቀ በኋላ የማጣሪያ ጥያቄ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

3) ባለሥልጣኑ በማናቸውም ጊዜ ከክርክሩ ጋር በተያያዘ ትእዛዝ ከማስጠቱ በፊት ተከራካሪን ወይም ችሎታ አለው ብሎ የሚገምተውን ማናቸውም ሰው በክርክሩ ላይ ወሳኔ ለማስጠት አስፈላጊ ሆኖ ያገኘውን የሰነድ ማስረጃ ወይም ማናቸውንም ቁሳቁስ፣ ናሙና ወይም ምርት እንዲያቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

15. ጊዜን ስለማራዘም

1) ባለሥልጣኑ በሚወስናቸው ሁኔታዎች መሠረት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብለት ወይም በሌላ በቂ ምክንያት ሌላ ቀነ ቀጠሮ ሊይዝ ይችላል፡፡

2) ባለሥልጣኑ ባለጉዳዩ በሚያቀርበው ተገቢ እና ምክንያታዊ ጥያቄ የጊዜ ማራዘሚያ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

16. የባለጉዳይ መቅረት

1) ክርክሩን ለማስማት በተቀጠረበት ቀን ማንኛውም ባለጉዳይ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በባለጉዳዩ አለመቅረብ ምክንያት ክርክሩን ወድቅ ሊያደርገው ወይም ባለጉዳዩ በሌለበት ክርክሩን ማየቱን ሊቀጥል ይችላል፡፡

2) ባለጉዳዩ ባለመቅረቡ ምክንያት ክርክሩ ወድቅ የተደረገ እንደሆነ ወይም ባለጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ከተወሰነ ቅሬታ ያለው ወገን ክርክሩ ወድቅ በተደረገ በአምስት (5) የሥራ ቀናት

ውስጥ የተሰጠው ትእዛዝ እንደገና እንዲታይለት ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑ ባለጉዳዩ ላለመቅረቡ በቂ ምክንያት አለው ብሎ ካመነ ትእዛዙን እንደገና ሊያየው ይችላል፡፡

17. ክስን ስለማንሳት

1) አንድ ከሳሽ ክርክሩ ከመሰማቱ በፊት ወይም በኋላ በማናቸውም ጊዜ ባለሥልጣኑን በጽሑፍ በማስታወቅ ክሱን ሊያነሳ ይችላል፡፡

2) ከሳሽ ክሱን እንዳነሳ ባለሥልጣኑ ተገቢ መስሎ የታየውን ከወጪና ከማካካሻ ጋር የተያያዘ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

ክፍል አምስት
ስለባለሥልጣኑ ውሳኔ

18. የባለሥልጣኑ የውሳኔ አሰጣጥ

1) ባለሥልጣኑ የክርክር መስማቱ ሂደት ባበቃ በአስራ አምስት (15) የስራ ቀናት ውስጥ ምክንያቶቹን በማስፈር ውሳኔውን በጽሑፍ መስጠት አለበት፡፡

2) የባለሥልጣኑ ውሳኔ ቀኑ ተገልጾ በዋና ዳይሬክተሩ መፈረም አለበት፡፡

3) የክርክሩ መስማት ሂደት ከውሳኔው ኮፒ ጋር በባለሥልጣኑ ሰብሳቢ አፊሰር በተረጋገጠና በተፈረመ ሰነድ እንደ እውነተኛና ትክክለኛ የክርክር ሂደት እና ውሳኔ በመዝገብ እንዲያያዝ መደረግ አለበት፡፡

4) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለጸውን ሰነድ የተረጋገጠ ቅጂ ለእያንዳንዱ ባለጉዳይ መላክ አለበት፡፡

5) ባለሥልጣኑ የጉዳዩን አስቸኳይነት ወይም በሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ጉዳዩ በመታየትና ውሳኔ በመጠበቅ ላይ እያለ ጊዜያዊ የዕግድ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

19. ውሳኔን ይፋ ስለማድረግ

1) የክርክር መስማት ሂደት መዝገቦች በባለሥልጣኑ በሚገለጹ ምክንያቶች ሚስጥራዊ ወይም የተገደቡ በመሆናቸው ወይም በሌላ ምክንያት ለማንም ሰው እንዳይገለጹ ከተወሰኑት በስተቀር ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚያወጣቸውን ጊዜን፣ ቦታን እና የምርመራ ዘዴንና የምርመራ ክፍያን የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የክርክሩ መስማት ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ለማንኛውም ሰው ለምርመራ ክፍት መሆን አለባቸው፡፡

2) ባለሥልጣኑ ያያቸውንና ውሳኔ የሰጠባቸውን ክርክሮች በድረ-ገጹ እና/ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

20. የውሳኔው ተፈጻሚነት

በባለሥልጣኑ የተሰጠ ውሳኔ ባለጉዳዮቹ እንዲያውቁት ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በባለጉዳዮቹ ላይ ተፈጻሚ መሆን አለበት፡፡

21. በውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ

1) በባለሥልጣኑ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን በሕግ ጉዳዮች ላይ በሰላሳ (30) የስራ ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚ አካል ይግባኙን ማቅረብ ይችላል፡፡

2) በይግባኝ ሰሚ አካል ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል በሕግ ጉዳዮች ብቻ በስልሳ (60) ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ ይችላል።

ክፍል ስድስት
ማስማማት

22. በባለሥልጣኑ የሚደረግ ማስማማት

1) የክርክሩ ባለጉዳዮች ሁለቱም ክርክሩ እንዲታይላቸው ጥያቄ ማቅረባቸውን ተከትሎ ጉዳያቸውን በጋራ ስምምነት በሙሉም ሆነ በከፊል በቅን ልቦና ለመፍታት ዓላማ አድርገው ድርድር ሊደረግ ይችላሉ፡፡

2) ከዚህ በታች የተመለከቱ ሁኔታዎች ሲኖሩ ባለስልጣኑ ባለጉዳዮችን አለመግባባታቸውን በስምምነት እንዲፈቱ ሊጣራቸው ይችላል፤ –

ሀ) ሁለቱም ተካራካሪዎች ይህን ለማድረግ በግልጽ የተስማሙ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) የማስማማት ጥያቄ ባይቀርብለትም ባለሥልጣኑ ክርክሩን በቀና መንገድ በስምምነት ሚጨረስ ይቻላል የሚል እምነት ካለው፡ ወይም

ሐ) የሽማግሌ መፍቻ ጥያቄው ወድቅ ሲሆን እና ሁለቱም አካላት አማራጭ የሽማግሌ መፍቻ ሂደቶችን ይቀበላሉ ተብሎ ሲታሰብ ነው።

3) ባለሥልጣኑ ክርክሩን በስምምነት መፍታት እንደሚቻል ካመነ ሥልጣኑን በመጠቀም በዕቅድ የተያዘን የማስማማት ወይም መደበኛ የክርክር መፍቻ ሂደትን ሊያቆመው ወይም ሊያግደው ይችላል፡፡

4) ባለጉዳዩቹ በስምምነት የሚቋጩ ክርክር የሚጨረሻ እና ይግባኝ የማይጠየቅበት ለመሆኑ መስማማት አለባቸው፡፡

23. በስምምነት ጉዳዮችን ስለመፍታት

1) በባለሥልጣኑ በፀደቀ ሚሮሃ ግብር መሠረት ጉዳያቸውን በስምምነት የሚጨርሱበትን ጊዜ ለማራዘም ካልወሰኑ በስተቀር፣ የክርክሩ ባለጉዳዮች ድርድሩ በተጀመረ በአሥራ አራት (14) የስራ ቀናት ውስጥ ስምምነት ላይ መድረስ አለባቸው፡፡

2) ባለጉዳዮቹ ክርክራቸውን በስምምነት ለሚጨረስ ከተስማሙ ቢያንስ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ያካተተ የስምምነቱን ዝርዝር ድንጋጌዎች ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፤

ሀ) በባለጉዳዩቹ መካከል ስለተደረሰው ስምምነት የሚያሳይ ግልጽ መግለጫ እና

ለ) በባለጉዳዩቹ መካከል ስለተደረሰው ስምምነት አፈጻጸም ዝርዝር የጊዜ ሰሌዳ፡፡

3) የባለጉዳዮቹ ስምምነት ለባለሥልጣኑ ከቀረበ በኋላ ባለሥልጣኑ የስምምነቱን ዝርዝር ድንጋጌዎች ከተቀበለ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለጉዳዮቹ ማሳወቅ አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ የባለጉዳዮቹን ስምምነት እንዳፀደቀው ክሱን ይዘጋዋል፡፡

4) በባለጉዳዮቹ መካከል የተደረሰ የማቻቸወም ስምምነት ዝርዝር ጉዳዮች በባለሥልጣኑና በባለጉዳዮቹ በጋራ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ በስተቀር በባለጉዳዮቹ ለሕዝብ ይፋ መደረግ የለባቸዉም፡፡

5) የዚህ አንጽ ንዐስ አንቀጽ (4) ቢኖርም ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ በማሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ የስምምነቱን ወጤቶች ለሕዝብ ማነወቅ ይችላል፡፡

6) ባለጉዳዮቹ በማቻቸወም ወይም በሁሉም ጭብጦች ላይ ስምምነት ላይ ያልደረሱ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ በመርሃ ግብር የተያዘወን ማከማማት ወይም የክርክር መፍቻ ሂደት እንዲጀመር ወይም እንደገና እንዲጀመር ሚድረግ አለበት፡፡

ክፍል ሰባት

ሕግ ማስፈጸም እና ሕግ ማክበር

24. ሕግ ማክበር

ባለስልጣኑ ባለፍቃዶች የአዋጁ እና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎችን ማክበራቸዉን ይቆጣጠራል፡፡

25. ሕግ ማስፈጸም

1) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ፥ አዋጁ እና ያጸደቃቸዉን መመሪያዎችን መነረት በሚድረግ ባለፍቃድ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጥሷል ብሎ ከወሰነ፤ በአዋጁ አንቀጽ 52 መነረት እርምጃ የሚወስድ ሲሆን እርምጃው
   ሀ) የገንዘብ ቅጣት ወይም ካሳ እና/ወይም
   ለ) የፈቃድ ማገድ/ማነረዝ፤ ነው፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ የሚወስደው እርምጃ እና ቅጣት የሚጥለው በአዋጁ አንቀጽ 52(6) መነረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ሲሆን በዚህ ደንብ የትኞቹ መተላለፎች የፈቃድ ማነረዝ፥ ማገድ እና ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደሚያስከትሉ የሚያመለክት ሲሆን ቅጣቶችን ለይቶ የሚያስቀምጥ እና የሚጣለው የመቀጮ ገንዘብ መጠን ይወስናል፡፡

ክፍል ስምንት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

26. የባለሥልጣኑ ኃላፊነት

ባለሥልጣኑ ይህን መመሪያ መሠረት አድርጎ ከሰጠው ወሳኔ ጋር በተያያዘ ለሚፈጸም ወይም ሳይፈጸም ለታለፈ ድርጊት ለማንኛወም ወገን ተጠያቂ አይሆንም፡፡

27. ማሻሻያ

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማንኛወም ግዜ ሁለንም ባለፍቃዶች አስቀድሞ በማነወቅ እና በአዋጁ ደንጋጌዎች መነረት የባለድርሻ አካላት የወይይት መድረክ በማዘጋጀት ይህን መመሪያ ማሻሻል ይችላል፡፡

28. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ…. ቀን 2013ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ …………ቀን 2013 ዓ.ም

ኢንጂነር ባልቻ ሬባ
የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር